የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
ETHIOPIAN PEOPLES REVOLUTIONARY PARTY (EPRP)

# ለኢሕአፓ የቀድሞ አባላት ጥሪ

ኢሕአፓ በሶስተኛው የፓርቲው ጉባኤ የቀድሞ አባላቱን የሚያሰባስብ ግብረ ሃይል እንዲቋቋም ከወሰነ ጀምሮ፣ የቀድሞ አባላቱን ለማሰባሰብ በአጽንኦት ይሰራ እንደነበር ከዚህ ቀደም በአትላንታ፤ በዋሽንግተን ዲሲና በሎስ አንጀለስ የተካሄዱት ስብሰባዎች ምስክሮች ናቸው።

በአለፈው ዓመት በሚያዚያ ወር 2006 የተካሄደው ዓራተኛው የፓርቲ ጉባዔ፤ ያለፈውን ጥረት ከመረመረና ካጤነ በኋላ፤ የቀድሞ አባላትን ለማሰባሰብ የሚደረገው ጥረት ተገቢና አስፈላጊ መሆኑን በማስረገጥ፤ ጥረቱን የሚያካሂደው አካል፤ በግብረ ሃይልነት ደረጃ በቀጣይነት የሚሰራ የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ንዑስ ኮሚቴ ሆኖ እንዲዋቀር ወስኗል።

ባንዳንድ አካባቢዎች፤ የድሮ አባላትን ለማሰባሰብ የሚደረገው ጥረት ከምን የተነሳ ነው የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ እንደሚችል ይታወቃል። መልሱ ግን ቅልብጭ ብሎ የሚታይ ግልጽ ጉዳይ ነው።

1. የቀድሞ አባላት ከአፍላ ዕድሜአቸው ጀምረው በትግል ተወልደው በትግል ያደጉ፤ በትግል የተፈተኑ፤ መከራና ስቃይ የተቀበሉ፡ የደሙና የቆሰሉ ናቸው። ስለሆነም ድርጅቱም፤ ትግሉም የነሱ ነው።

2. የቀድሞ አባላት፤ አብረው ከድርጅቱ ጋር፤ ከጫንቃቸው ያላወረዱት ከባድ የሃላፊነት ሸክም አለባቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በሃላፊነት ያሸከማቸው አገሪቱን ከድህነትና ከበሽታ አባዜ የማላቀቅ፤ የሃገሪቱን ሉዓላዊነትና የሕዝቧን አንድነት ሊያስከብር የሚችል፤ ለሕግ ተገዢ የሆነ፤ ማሕበራዊ ፍትህንና እኩልነትን ያካተተ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የማምጣትና የመገንባት ቃልኪዳናቸውን የማክበርና ሃላፊነታቸውንም መወጣት አሁንም ይጠበቅባቸዋል።

3. ባለፈው የትግል ጉዞአችን የጭቆናና የግፍ ሥራዓቶችን ካሰፈኑ ገዥዎች ጋር እንዲሁም ከጠባብ ብሔረተኞች ጋር በከተማና በገጠር ሲፋለሙ የወደቁ የጀግኖች ደም አሁንም እየተጣራ ነው።

4. እነዚያ በጨርቃነታቸው ትግሉን የጀመሩ ወጣቶች፤ ባሁኑ ጊዜ በትግልና በዕድሜ የበሰሉ ሙሁሮች፤ የዕድሜ ባለጸጋ አዛውንቶች ስለሆኑ ባሁኑ ሰዓት ውስብስብ ለሆነው የትግል ጉዞ ሊያበረክቱት የሚችሉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

5. እነዚህ የኢሕአፓ የቀድሞ አባላት ወደር የሌለዉ የሕዝብና የሃገር ፍቅር ስላላቸዉ መሰባሰባቸዉ ለሃገራችንና ለህዝባችን ከፍተኛ ጸጋ ነዉ።

ይህ እንዳለ ሆኖ፤ ባሁኑ ሰዓት አገሪቱ ያለችበት ሁኔታ ለዚህ የድሮ አባላትን መልሶ የማሰባሰብ ጥሪ ተጨማሪ ክብደት ይሰጠዋል፤

1. ኢትዮጵያ በባህልዋንና በአንድነቷ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ባደረሰ አሸባሪ አምባገነን ቡድን ሥር እየደቀቀች ባለችበት፣ የተቃዋሚውን ጎራ ጠባብ ብሔርተኞች ባጨናነቁበት፤ ባንጻሩ ደግሞ ጠባብ ብሔረተኞችን እንዋጋለን በሚል ከኛ ሌላ ኢትዮጵያዊ የለም በሚሉ የተሳከሩና የተዘበራረቀባቸዉ ወገኖች ትግሉን እያደናቀፉ ባሉበት፤ ስለሆነ ሃገራችን በሚያሰጋ ሁኔታ ባለችበት፤

2. ዘግናኝ በሆነ ድህነትና አስከፊ በሆኑ ኤይድስ/ኤች አይ ቪ፤ ወባ የመሳሰሉ በሽታዎች መሃል በመጠበስ ህዝቧ እንደ ቅጠል በሚረግፍበት ወቅት፤

3. ራሱን ከሕግ በላይ ባስቀመጠዉ አምባገነንና አሸባሪ ቡድን የሚመራው የህወሓት/ኢህአደግ ኢዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከግንቦቱ ምርጫ ወዲህ ፍጥጥ ባለ መልኩ አረመኒያዊ በትሩን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ባነሳበት ጊዜና ሕዝቡም በግንቦቱ ምርጫ የተቀዳጀውን ድል አላስነጥቅም በማለት ያመራር ያለህ እያለ በመጮኽ ትግሉን እየቀጠለ ባለበት ሰዓት፤ ያታሪካዊ ትውልድና ከትውልዱም መሐል የበቀለዉን ኢሕአፓን መስርተዉና ተቀላቅለዉ የታገሉት አባላት ዛሬ ፊታቸውን ሊያዞሩ አይገባም። ጭራሹን፣ በጀግንነት እንዳለፉት ጓዶቻቸው ‘ ለዘመናትን ‘ እየዘመሩ ትግሉን ማፋፋምና ከግቡ ማድረስ ይጠበቅባቸዋል። ኢሕአፓ ዉስጥ በአባላቱ መሐል የተፈጠሩ ችግሮችን፣ የተነሱ ጥያቄዎችን በዉይይት እልባት ሰጥቶ ማለፍ ይጠበቅብናል።

4. በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝባችንና ሃገሪቱ የሚገኙበትን ሁኔታ፤ አላላውስ ያሉትን ችግሮች በጥሞና ስንመለከታቸው፤ የኢሕአፓ መላው አባሎቹ፤ የድሮዎቹ ሆኑ አሁን ያሉት፤ ራሳቸው ባደራጁት ሆኖም በመራቸው ኢሕአፓ ሥር ካልተሰባሰቡ ትግሉ ተገቢውን ውጤት ሊያስገኝ መቻሉ አስተማማኝ አይሆንም። እምነት፣ ትልቅ ራዕይ፣ የሕዝብ ፍቅር፣ የትግል ልምድ፣ ለመሰዋእትነት ዝግጁነት፣ ሥነምግባርና ሥነሰርዓት ያለው፣ በዚህ ላይ ዕውቀትና ተመክሮ የጨመረ ሃይል፣ ለሃገሩ ቤዛ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ ግንዛቤ በመነሳትም ነው ኢሕአፓ ይህን የመሰባሰብ ጥሪ አሁንም እንደ አምናው የሚያስተላልፈው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል፣ በበለጠ መስዋዕትነት ግቡን ይመታል !
እናቸንፋለን !